**ይድረስ፡-**
**ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት!**

---

**<u>እንድታውቁት ያህል!</u>**

**የኢትዮጵያ Orthodox ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፡**
**ኹለት፡ የሊቃነ ካህናት ጉባኤዎቿ (Synods) በመወጋገዛቸው፡**
**በቀኖናዋ (በመንፈሳዊ ሕጓ) መሠረት፡**
**በአገር ውስጥና በውጭ አገር ያለው፡ <u>ክህነታዊ አገልግሎቷ፡</u>**
**በአኹኑ ጊዜ፡ መቋረጥ ብቻ ሳይኾን፡ ቆሟል፤ የለም፡፡**

---

**በቤተ ክህነት ውስጥ የተፈጠረውን፡**
**ይህን የመሰለውን፡ እጅግ አሳሳቢ ችግር ለመፍታት ደግሞ፡**
**ሥልጣኑና መብቱ ያለው፥ በኃላፊነት ተጠያቂውም፡**

# <u>የኢትዮጵያ ቤተ ሕዝብ</u>

**መኾኑን፡ የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታችን፡ ደንግጎታል፡፡**

**እንደኢትዮጵያ ሥርዓተ ሃይማኖት፡**
**የቤተ ክርስቲያኗ ካህናትና ምእመናን፡ በአባልነት የሚሳተፉበት፥**
**ቤተ ክህነቱንና ቤተ ምልክናውን ያስገኘው፥**
**ዋናው ግንዱ ዘርፍ፡ ይኸው ቤተ ሕዝቡ በመኾኑ፡**
**በአኹኑ የእርስ በርስ መወጋገዝ ምክንያት፡ ለተፈጠረው ችግር፡**
**ተገቢ የኾነውን መፍትሔ፡**
**በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ ከእግዚአብሔር ጠይቆ ለመቀበል፡**

## ራሱን በንስሓ አስተካክሎ፡

# ባስቸኳይ መሰብሰብ ያለበት፡

## ይኸው ቤተ ሕዝብ ነው፡፡

---

**ታዲያ! <u>ቤተ ሕዝቡ፡</u> በሃይማኖቱና በቤተ ክርስቲያኑ ላይ፡**
**ይህ ኹሉ ጥፋትና ጥቃት፥ ጉዳትም ሲደርስ ምን ይጠብቃል?**

---

በስመ እግዚአብሔር  አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፥ አሐዱ አምላክ፤

በስመ እግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ አንበሳ መዋኢ፡ ዘእምነገደ ይሁዳ፥ ሥርዉ ለዳዊት፥ ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ፥ ንጉሠ ጽዮን  ወንጉሠ ነገሥት ወንግሥታት ዘኢትዮጵያ፤

በስመ እግዝእትነ ወእምነ ወመቅደስነ ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፥ እንተ ይእቲ ሀገሪትነ ኢትዮጵያ፡ ዘታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር፡ በእንተ ኵሉ ዓለም፥ ንግሥተ ጽዮን ወንግሥተ ነገሥት ወንግሥታት ዘኢትዮጵያ።

## መግቢያ

ሦስቱ የእግዚአብሔር መንግሥት አካላውያን ዘርፎች የኾኑት፡ የኢትዮጵያ ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ምልክናና ቤተ ክህነት፡ በአኹኑ ጊዜ፡ በመለኮታዊው ሥልጣን ተወግዘው ይገኛሉ። ይህም የኾነው፡ በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. የተካኼደውን የደርግ አብዮት አነሣሥተው በመደገፋቸውና በመቀበላቸው፥ እስካኹንም፡ በዚሁ አቋማቸው ጸንተው፡ በግብረ አበርነት በመቀጠላቸው ነው። ይኸው ድርጊታቸው፡ በእግዚአብሔርና በሥርዓቱ ላይ፡ የክህደት፥ የዓመፅና የአምልኮ አመንዝራነት ኃጢአት ኾኖባቸዋልና። ስለዚህ፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፡ እስከዛሬ፡ በዚሁ ኹኔታቸው እንደቀጠሉ ናቸው።

ከዚሁ ኃጢአታቸው፡ በተገቢው የንስሓ ቀኖና ተመልሰው፡ ከመለኮታዊው ውግዘት እስካልተፈቱ ድረስ፡ በዚህ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት (ከዚህ በኋላ፡ "አገልግሎታችን" እየተባለ በሚጠቀሰው) ዘንድ፡ ተቀባይነት ሳይኖራቸውና እውቅናን ሳያገኙ የቆዩ፥ ወደፊትም የሚቆዩ መኾናቸውን፡ እናንተ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ታውቁታላችሁ።

## ጠንቀኛው ችግር

ይህን ቍም ነገር፡ ለጽሑፋችን መግቢያ አድርገን ከጠቀስን በኋላ፡ ቀጥለን፡ ለዚህ መልእክት፡ መነሻ የኾነንን ምክንያት እንገልጻለን፤ ይኸውም፡ በዚህ አስፈሪ ኹኔታ ላይ ከሚገኙት፡ ከእነዚህ ሦስት የአቋም ዘርፎች፡ አንዱ የኾነውን፡ ቤተ ክህነትን የሚመለከተው ጉዳይ ነው።

ይህ፡ የቤተ ክህነቱ ዘርፍ፡ ቀደም ብሎ ከተዘፈቀበት፡ ከላይ ከተገለጸው፡ ከዚያ ታላቅ ኃጢአቱ፡ ገና፡ በንስሓ ሳይነጻና ከውግዘቱ ሳይፈታ፡ አኹን ደግሞ፡ ከዚሁ ፍዳው የተነሣ በወረደበት፡ እጅግ አሳሳቢና አጣዳፊ በኾነ፡ በሌላ፡ የባሰ ችግር ተተብትቦና ተቀፍድዶ፡ እነሆ፡ ሲወራጭ ይታያል።

ይህን፡ የቤተ ክህነቱን ትክክለኛ ኹኔታና ገጽታ አጋልጦ ያወጣው፡ በውስጡ የተፈጠሩት፡ ኹለት ተጻራሪ የሊቃነ ካህናት ጉባኤዎች (Synods) ቀደም ብለው ያሳለፉት፡ የመጀመሪያው፡ የእርስ በርስ ውግዘታቸው ሳይበቃቸው ቀርቶ፡ ዛሬ፡ እንደገና የደገሙት፡ ከባድ ጠንቅን ያስከተለው፡ ኹለተኛው መወጋገዛቸው ነው፡፡ የዚህ ጠንቀኛ ድርጊታቸው አበጋዝ የኾነው፡ ርኩሱ መንፈስ፡ በረቂቅ ኃይሉ፡ እኒህ ኹለት ተፎካካሪ ጠበኞች፡ በመካከላቸው እጅግ የመረረውንና የከረረውን መቃቃር፡ ሲያካኺዱ እንዲቆዩ ካደረገ በኋላ፡ ይኸው ቅራኔያቸው፡ ውስጥ ውስጡን፡ እየተብላላና እየጋመ ቀጥሎ፡ በአኹኑ ጊዜ፡ መውደቂያቸው ለኾነው፡ ለኹለተኛው የእርስ በርስ ውግዘታቸው አበቃቸው፡፡ እርሱም፡ በዚህ ብቻ የሚወሰን አይደለም፤ ወደመጨረሻው የመጥፊያቸው ገደል ሊያደርሳቸው፡ ይኸው እየመራቸው ይገኛል፡፡

ይህ አሳፋሪ፡ የቤተ ክህነቱ ገመና፡ በመላው ዓለም ሕዝቦች ዘንድ ሳይቀር፡ ይፋ ኾኖ በመገለጡ፡ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን፡ ለታላቅ ትዝብትና ቅሌት ዳርጓቸው እንደሚገኝ፡ ለማንም ተመልካች ግልጽ ነው፡፡ ይኸው ቤተ ክህነት፡ ከፈጣሪው፡ ከኢየሱስ ክርስቶስና ከአምላክ እናት፡ ከድንግል ማርያም፡ በዋናነት የተቀበለው፡ የቃል ኪዳን ኃላፊነትና ተጠያቂነት ያለበት መኾኑ፡ ሊዘነጋ አይገባም፤ ይኸውም፡ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን፡ የማንነታቸው መታወቂያ የኾኑትን፡ ሃይማኖታቸውንና ምግባራቸውን፥ ሥርዓታቸውንና ቅርሶቻቸውን፡ በባለአደራነት የመጠበቁና የማስጠበቁ ድርሻው ነው፡፡

እንዲህ ከኾነ፡ ቤተ ክህነት፡ ይህን ከመሰለ ውርደት ላይ መውደቁ፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚለውን ዜጋ ኹሉ፡ በእርግጥ ሊያሳዝነው ይገባል፡፡ በዚህ፡ የቤተ ክህነቱ ዘርፍ ላይ፡ "በቍስል ላይ ቍስል" የኾነው፡ ይህን የመሰለው፡ የተባባሰ አደገኛ ችግር ወድቆበት ሳለ፡ "በዝምታና በግዴለሽነት የሚመለከት፡ ተቈርቋሪ ኢትዮጵያዊ፡ ይኖራል!" ብሎ መገመቱም ያዳግታል፡፡ እናንተ፡ እውነተኞቹ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ለጉዳዩ የተለየ ትኵረትን ሰጥታችሁ ትጸልዩበት ዘንድ፡ የኹኔታውን አስከፊነት ማሳወቁ፡ አግባብ ኾኖ ስላገኘነው፡ አገልግሎታችን፡ ይህን መልእክት ሊያስተላልፍላችሁ ተገድዷል፡፡

## አስደንጋጩ እውነታ

መለኮታዊ የኾነውን፡ ከፍተኛ ቍም ነገር የያዘው፡ የዚህ መግለጫ ልዩ መልእክት፡ እነሆ፡ ከዚህ በሚከተለው አጭር ቃል ቀርቧል፦

በአገር ውስጥም ኾነ፡ በውጭው አህጉር የሚገኙት፡ ኹለቱ የሊቃነ ካህናት ጉባኤዎች፡ ከላይ የተገለጸውን፡ የክህደት፥ የዓመፅና የአምልኮ አመንዝራነት ኃጢአታቸውን ቀንበር እንደተሸከሙና በመለኮታዊው ውግዘት እንደታሠሩ በሚሠቃዩበት ጕሥቍልናቸው ይገኛሉ፡፡ ይህን በመሰለው አሠቃቂ ኹኔታ ላይ እያሉ፡ አኹን ደግሞ፡ አንዱ፡ በሌላው ላይ፡ ኹለተኛውን፡ የእርስ በርስ፡ የውግዘት ውሳኔ፡ እነሆ አሳለፉ፡፡

በዚህ ምክንያት፡ ኹለቱም የሊቃነ ካህናት ጉባኤዎች፡ ማለትም፡ በየውስጣቸው ካሉት፡ ከሊቃነ መናብርቱ እጨጌዎችና ከአባሎቻቸው ሊቃነ ካህናቱ (Patriarchs & Papasses) ጋር፡ ከየክህነት ሥልጣናቸው ተሽረዋል፤ ማዕርጋቸውንና ሌሎቹን መንፈሳውያን መብቶቻቸውንም ኹሉ አጥተዋል።

ይህ ውሳኔ፡ በኹለቱም የሊቃነ ካህናቱ ጉባኤዎች አባሎች ላይ የጸናባቸው፡ እያንዳንዳቸው፡ በየግላቸውና ኹሉም፡ በኅብረት፡ ከባዕዳኑ ተቀብለው በሚመሩበትና በሚተዳደሩበት፡ ፍትሕ መንፈሳዊ በሚባለው፡ በፍትሓ ነገሥቱ አንደኛ ክፍል ውስጥ በተደነገገው ቀኖና (ሕግ) መሠረት ነው፤ ለዚህ አድራጎታቸው፡ ይህን ብይን ለመስጠት፡ ይኸው፡ የራሳቸው ቀኖና፡ በቂ ኾኖ ስለተገኘ፡ እነርሱ የካዱትንና ያመፁበትን መለኮታዊውን፡ የኢትዮጵያ ሥርዓተ ሃይማኖት፡ ለጊዜው፡ እዚህ ላይ መጥቀሱ የማያስፈልገን ኾኗል።

ደግሞም፡ ይኸው የውግዘት ውሳኔ ሊጸናና ተፈጻሚነትን ሊያገኝ የሚገባው፡ በኹለቱ የሊቃነ ካህናት ጉባኤዎች ውስጥ ባሉት አባሎቻቸው ሊቃነ ካህናት ዘንድ ብቻ ሳይኾን፡ ለእኒህ ሊቃነ ካህናት ሥልጣነ ክህነትና ማዕርግ፡ እውቅናን ሰጥተው በተቀበሏቸው ካህናትና ምእመናንም ዘንድ ጭምር ነው።

ከዚህ የተነሣ፡ በአኹኑ ጊዜ፡ በአገር ውስጥና በውጭ አገር ያለችው፡ የኢትዮጵያ Orthodox ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፡ ክህነታዊና መንፈሳዊ አገልግሎቷን፡ ለምእመናኗ ለማበርከት የሚያስችላትን ሥልጣን አጥታለች። ይህም፡ "በእነዚህ፡ ኹለት የሊቃነ ካህናት ጉባኤዎች ሥልጣንና አመራር ሥር ባሉት፡ በየሰበካው አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ፡ ሥርዓተ ቅዳሴና ሥርዓተ ጥምቀት፥ ሥርዓተ ተክሊልና ሌላውም፡ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የሚገኝበት መንፈሳዊ አገልግሎት ሊካኼድ አይቻልም!" ማለት ነው።

ይህ፡ የየውግዘታቸው ውጤት ሲብራራ፡ እንዲህ የሚለውን እውነታ፡ በበለጠ አረጋግጦ፡ ገሃድ ያደርገዋል፡- በእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ፡ በኹለቱም የሊቃነ ካህናት ጉባኤዎች አባሎች፥ ወይም፡ በማንኛውም፡ በእነርሱ ሥር በሚመራና በሚተዳደር ካህን፡ ሠራዒነትና ተራዳኢነት የሚካኼደው፡ ማናቸውም ዓይነት ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ሥርዓት፥ የሚጸለየው ጸሎትና የሚቀርበው ማዕጠንት፡ ወደፈጣሪ አያርግም፤ በምሥጢረ ጥምቀት፡ ከእግዚአብሔር፡ በመንፈስ ቅዱስ የሚገኘው ኹለተኛው ልደትና በቅዳሴ ጊዜ የሚዘጋጀው፡ የቅዱስ ቊርባን መሥዋዕት፥ እንዲሁም፡ በምሥጢረ ተክሊል የሚፈጸመው የጋብቻ አንድነትና የመሳሰሉት ሥርዓታት ኹሉ፡ ምትሓት እንጂ፡ እውን አይኾኑም። በድፍረት የሚደረግ ቢኖርም፡ አይሠምርም።

እዚህ ላይ፡ ለዚህ የውድቀት ፍጻሜ፡ መሠረቱና መነሻው፡ በአገር ውስጥ ያሉትና ወደውጭ አገር የተሰደዱት ካህናቱና ምእመናኑ መኾናቸውን መግለጽ ተገቢ ይኾናል። የዚህን ነገር እውነተኛነት ለማረጋገጥ ሌላ ማስረጃ አያስፈልግም፤ እኒህ ካህናትና ምእመናን፡ የኹለቱንም የሊቃነ ካህናት ጉባኤዎች አባሎች ሥልጣነ ክህነት፡ ምንም ዓይነት እንከን እንደሌለበትና በንጽሕና ጸንቶ እንዳለ አስመስለው፡ መስቀላቸውን በመሳለምና ጫማቸውን በመሳም፥ ቡራኬያቸውን በመቀበልና ስማቸውንም በጸሎት በማንሣት፡ እስካኹን፡ እውቅናን ሰጥተዋቸው መኖራቸው ይበቃል።

እኒህ ካህናትና ምእመናን: ይህን ታላቅ ኃጥኣት ሲፈጽሙ የቆዩት፥ አኹንም: እየፈጸሙ ያሉት: “ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ!” የሚለውን: የፈጣሪያቸውን መመሪያ ቃል: አውቀው፥ ንቀውና ቸል ብለው መኾኑን: የየራሳቸው ሕሊና ይፋረዳቸዋል፤ የሚፋረዳቸውም: ዛሬ: በውጭ ያሉት: የቀደሙት የሊቃነ ካህናቱ ጉባኤ አባሎች: ከደርግ ጋር: በይፋ በመተባበር ያደረጉትን፥ በአገር ውስጥ ያሉት: የዛሬዎቹም የሊቃነ ካህናቱ ጉባኤ አባሎች: ከባለጊዜዎቹ ጋር: በተባባሪነት እያካኼዱ ያሉትን የገሃድ ሥራ: በገዛ ዓይኖቻቸው አይተው ስለነበረ፥ ዛሬም እያዩ ስለኾነ ነው:: (ማቴ. ፯፥ ፲፭-፳::)

ነገር ግን: ይህ ኹሉ እየኾነ ያለው: “ኵሉ ዐረየ: ወኅቡር ዐለወ!” “በክህደቱና በዓመፁ: ኹሉም: ተስተካክለው አንድ ኾኑ!” የሚለው አምላካዊ ቃል: በዘመናችንም ደርሶ ይፈጸም ዘንድ: ግድ ስለኾነ ነው:: እንደዚያማ ባይኾን ኖሮ፥ ወይም: ከካህናቱና ከምእመናኑ መካከል: አንድ: አስተዋይ ተመልካች እንኳ ተገኝቶማ ቢኾን ኖሮ: ከላይ እንደተገለጸው: እየራሳቸው ከሚያውቁት ጋር: የኹለቱም የሊቃነ ካህናት ጉባኤዎች አባሎች: በየበኩላቸው ይፋ ያወጡት: ያ ኹሉ የየራሳቸው የምስክርነት ቃል: በግዙፍ ማስረጃነቱ በበቃቸው ነበር:: እርሱም: አንዳቸው: የሌላውን ነውርና ወንጀል: ያለኃፍረት በመዘርዘር: በየፊናቸው የፈጸሟቸውን የግፍ ኃጢኣቶች ባስታወቁበት: በየውግዘታቸው የውሳኔ ጽሑፍ ውስጥ: የሰጡት ሐተታ ነው:: (መዝ. ፲፫፥ ፩-፫::)

መቸም: ከእግዚአብሔር ዳኝነት ማምለጥ የሚቻለው ማንም የለምና: እኒህ ካህናትና ምእመናን: ለዚህ ጥፋታቸውና በደላቸው: ተገቢ የኾነው ፍዳ ተከፍሏቸዋል፤ አኹንም: እየተከፈላቸው ነው፤ ይኸውም: እንደጌታችን ቃል: ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ባለበት ሥቃይ እንዲኖሩ የተበየነባቸውን ፍርድ: እነሆ: በመቀበል ላይ ስለሚገኙ ነው፤ ይህም እውነታ: መንጎቻቸውን: ለተኲላ አሳልፈው እንደሚሰጡ ምንደኞች በሚቆጠሩ: እኒህን በመሰሉ እረኞች እጅ በመውደቃቸው: ይኸው ተረጋግጦ ይታያል:: (ማቴ. ፳፭፥ ፳፬-፴::)

ይህ ኹሉ: የሊቃነ ካህናቱ ጉባኤዎች ክፉ ድርጊት: ማለትም: የእርስ በርሱ ውግዘት: ያስከተለው ውጤት: የእነርሱ ተከታይ በኾነ: “ሃይማኖታዊ ነኝ!” በሚል: በማንኛውም ሰው ዘንድ: በትክክል ሊታወቅ በተገባ ነበር፤ ከዚህ የላቀ: ሌላ አስጨናቂና ብርቱ ነገር ሊኖርበት ከቶ አይችልምና:: መንፈሳዊዉን ብቻ ሳይኾን: ሥጋዊዉንና ነፍሳዊዉን ሕይወቱን ጭምር: የሚመለከት ጠንቀኛ ጉዳይ ስለኾነ ነው::

እንግዴህ: የአገር ውስጡ የሊቃነ ካህናት ጉባኤ: በውጭ አገሩ የሊቃነ ካህናት ጉባኤ ላይ የሰጠው ውሳኔና ያሳለፈው ውግዘት፥ እንዲሁም: የውጭ አገሩ የሊቃነ ካህናት ጉባኤ: በአገር ውስጡ የሊቃነ ካህናት ጉባኤ ላይ የሰጠው ውሳኔና ያሳለፈው ውግዘት: በኹለቱም የሊቃነ ካህናት ጉባኤዎች አባሎች ላይ ብቻ ሳይኾን: የእነርሱ ተከታዮች በኾኑት ካህናትና ምእመናን ላይ ጭምር: የሚጸና ከመኾኑ በቀር: ሌላ ማማረጫ፥ ወይም: ማምለጫ የለም::

በኹለቱም ወገኖች በኩል የተደረጉት ውግዘቶች፡ በዚህ መልክ መጽናት ስለሚገባቸው፥ የኹለቱም ጉባኤዎች ሊቃነ መናብርትና አባሎች የኾኑት እጨጌዎቹና ሊቃነ ካህናቱ፥ እንዲሁም፡ በእነርሱ አመራርና አስተዳደር ሥር ያሉት፡ ካህናቱ ኹሉ፡ ሥልጣነ ክህነታቸውን ፈጽመው መገፈፋቸው፡ በእርግጥ እውን ኾኗል። ስለዚህ፡ እነዚያ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች፡ በረቂቁ መንፈሳዊ ባሕርያቸውና በገሃዳዊው አካላዊ ገጽታቸው፡ "በቤተ ክህነቱ ዘንድ የሉም፤ ከዚያ ተወስደዋል፤ ወደዚያ አይወርዱም፤ አይሰጡም" ማለት ነው።

## ለጠንቀኛው ችግር፡ ብቸኛው መፍትሔ

እንዲህ ከኾነ፡ የዛሬዎቹ ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ምልክናና ቤተ ክህነት፡ በቅዱሱ ኪዳን መሓላቸውና በእውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ አምልኳቸው ጸንተው ቢኾን ኖሮ፡ ይህን ለመሰለው ችግር ማስወገጃ ይኾናቸው ዘንድ፡ ጥንቱኑ፡ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን፡ ከፈጣሪያቸው በተሰጣቸው፡ ፍቱን መፍትሔ መጠቀም በቻሉ ነበር፤ ይህም መፍትሔ ተይዞ የሚገኘው፡ <u>በቤተ ሕዝባቸው</u> ዘንድ ነው፤ መፍትሔው፡ በሥራ ላይ የሚውለውም፡ በዚሁ፡ <u>በቤተ ሕዝባቸው</u> ነው። <u>"ቤተ ሕዝብ"</u> የሚባለውም፡ <u>በሰበካ ጉባኤዎች የተካተቱትን ካህናትና ምእመናን፡ በአባልነት የያዘው</u> ዋናው አካል ነው። በመለኮታዊውና በሃይማኖታዊው የአገር አቋምና ሥርዓት መሠረት፡ ለሥጋዊው አገልግሎት፡ ቤተ ምልክናውንና "ምሉካን" የሚባሉትን ባልደረቦቹን፥ ለመንፈሳዊው አገልግሎት ደግሞ፡ ቤተ ክህነቱንና "ካህናት" የሚባሉትን ባልደረቦቹን መርጦ የሚሠይመውና የሚያስተዳድረው፡ ግንዱ አካል፡ ይኸው <u>ቤተ ሕዝብ</u> ነው።

ይህ <u>ቤተ ሕዝብ፡</u> ለጠንቀኛው ችግር ማስወገጃ ኾኖ የሚያገኘውን መፍትሔ፡ በሥራ ላይ አውሎ፡ ለመልካም ፍሬ ለማብቃት የሚያስችለውን፡ መንፈሳዊውን መሣሪያ ያስታጠቀውና ሥልጣኑን ያቀዳጀው፡ ሉዓላዊው ምንጭ፡ መለኮታዊው የኢትዮጵያ ሥርዓት ነው። ይህን መለኮታዊ ሥርዓት በመከተል፡ በአኹኑ ጊዜ፡ በኹለቱ የሊቃነ ካህናት ጉባኤዎች መካከል የተፈጠረውን እጅግ አሳሳቢ ችግር ለመፍታት፡ ይኸው <u>ቤተ ሕዝብ፡</u> በእግዚአብሔር ዘንድ ያለው፡ የኃላፊነቱና የተጠያቂነቱ ድርሻ ይጠብቀዋል።

ስለዚህ፡ <u>የቤተ ሕዝቡ አባሎች የኾኑት፡ በአገር ውስጥም ኾነ በውጭ አገር የሚገኙት፡ የየሰበካው ጉባኤ ካህናትና ምእመናን፡</u> ከፈጣሪያቸው፡ በቃል ኪዳን በተሰጣቸው፡ በዚህ ሥርዓትና እርሱ ባቀዳጃቸው ሥልጣን በመጠቀም፡ የግዴታ ድርሻቸውን ሊወጡ ይገባቸዋል። ይህም፡ በቅድሚያ፡ <u>እኒህን ኹለት ተጻራሪ የሊቃነ ካህናት ጉባኤዎች፡ ለጊዜው በተወሰኑ ቦታዎች አስገልለውና አስጠብቀው፥</u> እነርሱ፡ <u>በቤተ ሕዝብነታቸው፡ በያሉበትና በኅብረት ሲሰባሰቡ ነው፤</u> ቀጥሎ፡ <u>"ስለስሜ በተሰባሰባችሁበት፡ እኔም በመካከላችሁ እገኛለሁ!" ባለው፡ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ መንበርነት፡ እንዲህ ተሰባስበው፡ ለዚህ ችግር ማስወገጃ ይኾናቸው ዘንድ፡ እርሱ፡ በመንፈስ ቅዱስ የሚያቀርብላቸውን፡ መለኮታዊ መፍትሔ ተቀብለው፡ በተግባር ላይ ሲያውሉት ብቻ ነው።</u> (ማቴ. ፲፰፥ ፲፱-፳።)

# የንስሓ ቀኖና አስፈላጊነት

ቤተ ሕዝቡ፡ መለኮታዊው የኢትዮጵያ ሥርዓት ባጐናጸፈው፡ በዚህ ሥልጣን ተጠቅሞ፡ አኹን፡ በቤተ ክህነቱ ውስጥ ለተፈጠረው ጠንቀኛ ችግር፡ ፍቱን የኾነውን መፍትሔ በማበርከት፡ እንዲህ ያለውን መልካምና ጣፋጭ ፍሬ፡ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን ሊያስገኝ ይችላል። ይኹን እንጂ፡ ቤተ ሕዝቡ፡ ለዚህ ችሎታ በቅቶ የሚገኘው፥ ማለትም፡ ራሳቸው፡ የቤተ ሕዝቡ አባሎች፡ ካህናቱም፥ ምእመናኑም፡ ለዚህ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ሥልጣን የሚበቁት፡ በአንድ መንገድ ብቻ ነው፤ ይህም፡ ከቤተ ክህነቱና ከቤተ ምልክናው ጋር፡ ተባባሪ ኾነው ከቆዩበት፡ ከታላቁ የክህደት፥ የዓመፅና የአምልኮ አመንዝራነት ኃጢአታቸው፡ በቅድሚያ፡ በተገቢው ንስሓ ተመልሰው ሊነጹ የሚያስፈልጋቸው መኾኑ ነው። ይህን፡ ቀዳሚ ግዳጃቸውን፡ ኹሉም ሊያውቁት ይገባቸዋል። የዚህ ንስሓቸው ሥርዓትና አፈጻጸሙ፡ በጾመ ኢትዮጵያ ጊዜ፡ ለሦስት ቀናት የሚደረገውን ቀኖና መስሎ ሊዘጋጅ ይችላል።

እንግዴህ፡ ይህ ኹኔታ፡ "የኢትዮጵያ Orthodox ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባሎች ነን!" ለሚሉ ካህናትና ምእመናን፡ ለወንዶቹም፡ ለሴቶቹም፥ ለአዛውንቱም፡ ለወጣቶቹም፡ እጅግ አሳሳቢና አስቸኳይ፡ የሞት ወይም የሕይወት፥ ያውም፡ የመንፈሳዊውን ህልውና የሚመለከት፡ ብርቱ ጉዳያቸው ሊኾን ይገባል።

ይህን መልእክት በሚመለከት፡ የሚያስፈልገውን፡ ማናቸውንም የምክር አስተዋጽዖ፡ ለቤተ ሕዝቡ ለማበርከት፡ አገልግሎታችን፡ ፈቃደኛነቱን፡ በዚህ አጋጣሚ ሊገልጽ ይወድዳል።

ስለመለኮታዊው የኢትዮጵያ የሃይማኖትና የአስተዳደር ሥርዓት፥ ስለንስሓው ቀኖና፥ ስለመሳሰሉትም ነክ ጉዳዮች፡ በዚህ፡ በአገልግሎታችን የጎዋ ሰሌዳ ውስጥ ያሉትን ልዩ ልዩ ማኅደሮች በመክፈት፥ ጽሑፎቹን በመመልከትና መጻሕፍቱን በማዘዝ፡ በበለጠ መረዳት የሚቻል መኾኑን እንገልጻለን።

ለኢትዮጵያና ለእኛ ኢትዮጵያውያን፡ ንጉሣችንና ንጉሠ ነገሥታችን፥ ካህናችንና ሊቀ ካህናታችን የኾነው ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንና እናታችን፥ አገራችንና ንግሥታችን ድንግል ማርያም ጋር፡ በቅዱስ ኪዳኑና በቅዱስ መንፈሱ፡ በያለንበት እየጠበቀን ሲመራን እንደኖረ ኹሉ፡ ዛሬና ወደፊትም፡ ይህን አመራሩን እንደማያጓድልብን እናምናለን!

\+ \+ \+